# የኦታዋው ወረቀቴ አበሳ

**ከ**
**ጌታቸው በጋሻው**

ኢትዮጵያ ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩና መልካም አስተዳደር እንዲመሰረት ለማድረግ እንዴት ይቻላል? ለሚሉት መንታ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በማሰብ በርካታ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና የእድገት ተቋሞች በመተባበር ሜይ 4 ቀን 2007 የካናዳ ዋና ከተማ በሆነችው ኦታዋ ውስጥ አንድ የክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት አዘጋጅተው ነበር። ይህንን ስብሰባ ለማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማድረግ ከሚጠቀሱት የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ውስጥ አንዱም በካናዳ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አስተባባሪ ኮሚቴ (SOCEPP-CANADA) ነው። በዚህ ስብሰባ ላይ የተለያዩ የካናዳ መንግስት መስሪያ ቤቶችን የሚወክሉ ባለስልጣናት ተገኝተዋል። ስብሰባውን ለማዘጋጀት ምክንያት ለሆኑ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ወይም የወደፊቱን በማመላከት ሊረዱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ኢትዮጵያውያኖችንና የኢትዮጵያ ጉዳይ ዓዋቂ የሆኑ የውጭ አገር ሰዎችንም ለማሰባሰብ ጥረት የተደረገበት ስብሰባ ነበር። እኔም ለዚህ ስብሰባ ከተጋበዙት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነበርኩ። ለዚህ ፅሁፍ መቅረብ ዋነኛው ምክንያት ከስብሰባው ውጭ፥ ማለትም ስብሰባውን ባልተካፈሉና በጉዳዩም ላይ የቅርብ ዕውቀት የሌላቸው ጥቂት ግለሰቦች በስብሰባው ላይ ስላቀረብኩት ወረቀት በርካታ አሳሳችና የስም ማጥፋት ዘመቻዎች በማድረግ ላይ በመሆናቸው ማብራሪያ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ነው።

*ጋባዦቹ እኔ እንድናገርበት የሰጡኝ ርዕስ "ከኢትዮጵያ የ97ቱ ምርጫ የተማርናቸው ቁምነገሮችና የወደፊት ዕይታ" የሚል ነበር። በዚሁ አጠቃላይ ርዕስ ስር አራት ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ እንዳተኩርም ነግረውኝ ነበር። እነሱም፥ (1) ምርጫው ፍትሃዊና ርዕታዊ ነበረን? ካልሆነስ ምን ጎደለ? (2) የፓርላማ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ እየሰራ ነው ወይ? (3) በኢትዮጵያ ውስጥ እርግጠኛ የፓርላማ ስልጣን ጋርዮሽ ይቻላልን? (4) ለወደፊቱ መሻሻልና እርዳታ የሚያስፈልግባቸው መስኮች ምንድን ናቸው? የሚሉ ነበሩ።*

በዚህ ፅሁፍ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ጥያቄዎች ባቀረብኳቸው አጠቃላይ መልሶች ላይ ምንም ክርክር ስላልተነሳ ወንጀዮቼ ለስድብና ለስም ማጥፋት በዋናነት በተጠቀሙበት በአራተኛው ጥያቄ ላይ አተኩራለሁ። ከወዲሁ ግን እንዲታወቁልኝ የምፈልጋቸው ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው፥ በዚህ ስብሰባ ላይ ያቀረብኩት ወረቀት ከህዝብ የተደበቀ ሳይሆን ከስብሰባው ማግስት (ሜይ 6) ጀምሮ በጽሁፍ የተበተነና በተለያዩ ድረ-ገጾች ላይ ወጥቶ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ እንዲያዩት የተደረገ መሆኑንና እስካሁንም በብዙዎቹ ድረ-ገፆች ላይ መኖሩን ነው። ሁለተኛው፥ ይህ ስብሰባ የተጠራው ኢትዮጵያ ውስጥ አስከፊ የፖለቲካ መብት ችግሮች ስላሉ እነኝህ ችግሮች እንዲወገዱ ለመርዳት እንፈልጋለን ብለው በተነሱ የውጭ አገር ዜጎች እንጂ ወትሮ የምናውቃቸው ህወሓትን የሚቃወሙ ኢትዮጵያውያኖች ያዘጋጁት ስብሰባ አለመሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው የካናዳ መንግስት ከህወሓት መንግስት ጋር ይሰራል። ስብሰባውን ካዘጋጁትና በስብሰባው ላይ ከተሳተፉት አብዛኞቹ የግብረ-ሰናይ ድርጅቶችና የእርዳታ ተቋሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በግልፅ የሚንቀሳቀሱና በህወሓት መንግስት ለመጠላትም ሆነ ለመባረር የማይፈልጉ ናቸው። ይህ የመንግስትና የአዘጋጆች የግንኙነት ሁኔታና የስብሰባው መድረክ፥ ማለትም የዲፕሎማቲክ መድረክ፥ የምንጠቀማቸውን ቃላትና አገላለጾች ከወትሮው የፖለቲካ ድስኩር የተለዩ እንዲሆኑ የግድ ይላል።

ለስብሰባው ባቀረብኩት ወረቀትና ባደረግሁት ንግግር ላይ፥

አንደኛ፥ የምርጫው ድምጽ ቆጠራ በውል ተጠናቅቆ ስላልተረጋገጠ በእርግጠኛ አሀዝ አስደግፎ ለመከራከር ቢያስቸግርም፥ የተለያዩ የምርጫ ታዛቢዎችን ግምትና ትንታኔ፥ እንዲሁም በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታ ገላጭ የሆኑትንና በተቃዋሚ የፖለቲካ ሀይሎቹ ቀርበው የነበሩትን የመፍትሄ ሀሳቦችን በማጣቀስ፥ የ97ቱ ምርጫ በተቃዋሚ ሀይሎች አሸናፊነት ሲጠናቀቅ የምርጫው ውጤት ግን በኅወሀት ተሰረቀ ብሎ ለመደምደም እንደሚያስችል፤

ሁለተኛ፥ህወሓት የማይፈልጋቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች፥ በተለይም እንደ ኢሕአፓና ኦነግ ያሉትን፥ እያገደና ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ለአገር እድገትና ሰላም እንደተባባሪ ከመቁጠር እንደ ጠላት እየተመለከተ የፓርላማ ዴሞክራሲ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰራ እንደማይችል፤

ሶስተኛ፥ ፓርላማው ነጻ የህግ አውጭ፥ የስልጣን መቆጣጠሪያና ማስተካከያ አካል እስካልሆነ ድረስ፥ ኅወሀት የፓርላማውን ህግ እንዳሻውና ለራሱ የሀይል ብልጫ እንዲሰጠው እያደረገ በሚቀያይርበት ሁኔታና ፓርላማውን ለራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም ህጋዊ ሽፋን እስከተጠቀመበት ድረስ የፓርላማ የስልጣን ጋርዮሽ በኅወሀትና በተቃዋሚ ሀይሎች መሀል ሊኖር እንደማይችል፤

በሰፊው ካሰረዳሁ በኋላ፥ በአራተኛው ክፍል ውስጥ፥ ያሉትን የፖለቲካ መብት ችግሮችን ለማስወገድ የሚከተሉት ስድስት ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው በግልጥ አስቀምጫለሁ:: እነሱም፥

(1) ለረጅም ጊዜ በእስር እየተንገላቱ ያሉት የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲለቀቁ፥
(2) የታገዱ የፖለቲከ ድርጅቶች፥ በተለይም ኢሕ አፓና ኦነግ፥ ህጋዊነታቸው ተረጋግጦላቸው የፖለቲካ ተግባሮቻቸውን በአገሪቱ ውስጥ ለመስራት እንዲችሉ፥
(3) የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጦችና የዜና አውታሮች የመናገርና የመጻፍ መብቶቻቸው ተከብረው ለመስራት እንዲበቁ፥
(4) እንደ ኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ያሉ የብዙሀን ድርጅቶች የሚደርስባቸው ወከባ ቆሞ የተመሰረቱባቸውን ዓላማዎች ለማራመድ እንዲችሉና የአገሪቱን የዴሞክራሲ ሂደት እንዲያግዙ፥
(5) ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የብዙሃን ማኅበሮች ያካተተ የብሄራዊ ዕርቅ ጉባዔ እንዲጠራና አወዛጋቢ ሆነው ባሉት የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ንግግር እንዲያደርጉ፥
(6) ሁሉም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባለጉዳዮች በ2002 (በ2010 በፈረንጅ) ለሚደረገው ምርጫ ሊስማሙባቸው በሚችሉባቸው የምርጫ ደንቦችና ዝግጅቶች ላይ ውይይት እንዲጀምሩ የሚሉ ናቸው::

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ "ላም ባልዋለበት..." እንዲሉ በዚህ ስብሰባ ላይ መገኘቴን ባለመውደድም ይሁን በሌላ ድብቅ ምክንያት ጥቂት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሳታፊ ነን የሚሉ ግለሰቦች (በተለይም ጥቂት የአምባገነኑ የኢሕአፓ ክፍል አባላት) ያቀረብኳቸውን የትንተናና የአቋም ነጥቦች አንድ በአንድ ለይተው ስህተቶቹንና ጉድለቶቹን ከማጋለጥ ይልቅ “ኦታዋ ሄዶ ያቀረበው ወረቀት ለወያኔ እጅ መንሻ ነው፥ ከወያኔ ጋር ለመስራት ይቻላል ብሏል፥ በ2002 ምርጫ መሳተፍ አለብን ይላል፥ ተንበርካኪ አቋም ነው፥ ወዘተ” በሚሉ ከንቱና ጊዜ ባለፈበት የስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ ተሰማሩ:: በዚህን ጊዜ በኔ በኩል በቅድሚያ "ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች ለህወሓት እጅ መስጠት፥ መስገድ ወይም መንበርከክ የሆኑት የትኞቹ ናቸው? ዬት ላይ ነው ከህወሓት ጋር መስራት ይቻላል ወይም በ2002 ዓ. ም. ምርጫ እንሳተፋለን የሚል ሃሳብ ያቀረብኩት? ምናልባትም ለኔ ያልታየኝና ለናንተ የተገለፀላችሁ ካለ ጠቁሙኝና ልማር" ስል ደፍሬ ጠየቅሁ:: ምላሹ ግን ይበልጥ መወንጀል ሆነ:: ሰብዕናዬ ላይ መንጠላጠልም ተከተለ::

ለመሆኑ ህወሓት ከላይ የተጠቀሱትን ስድስት ሁኔታዎች ቢያሟላ፥ የለም ጥይት ካልተኮስን አይሆንም ብለን መገልገል አለብን? እነኝህ ሁኔታዎች ተሟልተውስ እውን የጥይት ተኩስ የሚያደርግስ አለ? የሚያደርግ አለ ቢባልም ህዝቡስ የሚቀበለውና የሚከተለው ይሆናል? ደግሞስ እነኝህ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ተብሎ ስለተጠየቀ ካልተኮስኩ ብሎ የሚገለገለው ክፍል ምን ጎደለበት? ጥይት ወይም ጠመንጃ ተነጠቀ? ዛሬ እውነታው የሚያረጋግጠው በተግባር የተደረገን የተጨበጠ ሁኔታን ወይስ ለስንት ዓመታት ከአሜሪካና ከአውሮፓ መዲናዎች ስንጋት የከረምነውን ባዶ ፉከራ? እውነቱ የቱ ነው?

የተካፈልኩበት ስብሰባ የአስተናጋጁ አገር መንግስት ተወካዮች፥ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፥ የግብረ-ሰናይና የእርዳታ ሰጭ ተቋሞች ባለስልጣናት የሚሳተፉበት የዲፕሎማቲክ መድረክ ነበር፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ መድረክ ላይ ደግሞ፥ ትንሽ ለመደመጥና አገራችንና ህዝባችንን ልትረዳ የምትችል አንዲት መልእክት እንኳን ለማስተላለፍ  ቃላት መምረጥና አነጋገርን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የተሰበሰቡት የውጭ አገር ሰዎች በአገራችን ሁኔታ ላይ ብዙ የሰሩ ስለነበሩ ምናልባት ብዙዎቻችን ከምንገምተው በላይ ስለኛ ያውቃሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ስላገሬ የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ ብሎ መገመትም ደካማነት ነው፡፡ ሁሉም የምንናገራቸውን ከማዳመጥም አልፈው መነሻውንና መድረሻውን ለመገመትም ይችላሉ ብዬ ጠርጥሬያለሁ፡፡ ስለዚህ፥ "ሰላም አገራችሁ ውስጥ እንዲመጣ ለመርዳት እንፈልጋለንና ምን ብናደርግ ይሻላል?" ብለው ህሳብ ለሚጠይቁን የውጭ አገር ሰዎች ከመቅፅበት “የለም ወያኔ በሰላም ስልጣን አይለቅምና ጠመንጃ ስጡን” ብዬ በዚያ መድረክ ላይ ለመጠየቅ እንደማልችል ሊረዱልኝ ያልቻሉ ወገኖቼ ለምን ሁኔታውን በብርቱ ለማጤን እንደማይፈልጉ ዛሬም ድረስ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል፡፡

ዋናው ቁምነገር ህወሓት ከላይ የዘረዘርኳቸውን ስድስት ሁኔታዎች ያለምንም ጣጣ ቢያሟላልን እግዜር ታደገን፥ ህወሓት ለደግ ተለወጠልን፥ ኢትዮጵያ የደም አውድማ መሆኗ ቀረ፥ ህዝባችን የሰላም አየር ተንፍሶ የእለት ጉርሱን ሊያሸንፍ በሚችልበት መንገድ ላይ ዋለ፥ ረሀብ ድህነት በሽታና ድንቁርና የድሮ ታሪክ ሆኑ፥ ብለን ከበሮ በደለቅን ነበር፡፡ ነገር ግን ህወሓት አያደርገውም፡፡ በስብሰባው ላይ የነበሩት የውጭ አገር ተሳታፊዎች ደግሞ ከቀረቡት ስድስቱ ነጥቦች ውስጥ የሚጥሉት ወይም የማይስማሙበት አንድም ነጥብ አልነበረም፡፡ ከስብሰባው በኋላ ይፋ በሆነው የጉባዔው ሪፖርት ላይ እንደተቀመጠው ስድስቱ ነጥቦች የጉባዔው የውሳኔ ነጥቦች አካል ሆነዋል፡፡ ታድያ፥ ህወሓት በነኝህ መሰረታዊ በሆኑ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች የማያምን ዘረኛና አምባገነናዊ መንግስት መሆኑን ማሳዬት ክፋቱ ምኑ ላይ ነው? ይልቁንም ለትግላችን እንደ አንድ በጎ አስተዋጽዖ የሚታይ ነበር - ወንጀዮቼ ቀና መንፈስና ቅን ልቡና ቢኖራቸው ኖሮ፡፡

የተሳተፍኩበት የኦታዋው ስብሰባ በዲፕሎማሲያዊ መስክ የሚካሄድ የሰላማዊ ትግላችን አንድ አካል ነው፡፡ ሰላማዊ ትግል ደግሞ የኢህአፓ አንዱ የትግል ስልቱ ነው፡፡ ኢህአፓ የሚያምንበት ሁለ-ገብ ትግል ሰላማዊ ትግልንና  የመሳሪያ አመጽን እንደ ሁኔታው እንደ አመቺነቱና አንደ ችሎታው አጣጥሞ የሚያስኬድ የትግል ስልት ነው፡፡ ኢሕአፓ ከጥንት ከመሰረቱ በሰላማዊ ትግል ያምናል፡፡ ደርግ በሰላማዊ መንገድ እንድትታገል አልፈቅድልህም ስላለው ነው እንጂ የአጥፍቶ መጥፋት አባዜ ኖሮት አይደለም ወደ መሳሪያ ትግል የገባው፡፡ ህወሓትም ቢሆን ከጥዋቱ ሊያጠፋው ቆርጦ የተነሳ በመሆኑና ይህንንም ፍላጎቱን ገና ስልጣን ሳይይዝ በመሞከሩ ነው እንጂ ኢሕአፓ በሰላም ገብቶ ለመስራት ያለውን ፍላጎቱን ያወጀባቸው ጊዜያትና ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡ ለዚህ ብዙ ሰነዶችንና  በራሱና በኢዴህቅ፥ እንዲሁም በኅብረት አባልነቱ የወሰዳቸውን አቋሞች በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነኝህ ሁሉ ደግሞ ትክክለኛ አቋሞች ናቸው፡፡ ታዲያ ዛሬ ምን የተለወጠ ነገር ኖሮ ነው የኔ የኦታዋ ስብሰባ ተሳትፎዬ እንደ መስመር ለውጥ የተቆጠረው? ለዚያውም የተጋበዝኩትና የተናገርኩት በድርጅቱ የአመራር አባልነቴ ሳይሆን በራሴ በግሌ ሆኖ፡፡

አገራችንን የማዳን ትግል የምናካሄደው በተራ ስድብና የስም ማጥፋት ዘመቻ ወይም በደርሶ ጀግና መሳይነትና በማይጨበጥ የጦርነት አታሞ ድለቃ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ብልህነትና የመሪነት ብቃት የሚለካው በተራ ቅጥፈትና አባላትን በማታለል ብልጣብልጥነትም አይደለም፡፡ የአገሪቱን÷ የአካባቢንና የዓለም አቀፋዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን እየተመለከቱና እያገናዘቡ አቅምንና ችሎታን እየመዘኑ የህዘቡን ትግል ከትክክለኛ ፈሩ ለማቆዬት መቻሉ ነው ታላቅነት፡፡ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም አባላትን መዋሸትና ማደናበር÷ ለዚያውም የአማኝ አባላትን የወደፊት ዕድልና ህይወት በቆይታ መያዝ ታላቅ ወንጀል ነው፡፡

ላንድ አፍታ የ2002 ዓ. ም. ምርጫን ጉዳይ እናንሳ፡፡ የሚያሳዝነው ወንጀዮቹና ሰብዕናዬ ላይ ተንጠልጣዮቹ "የግንቦቱን ድል ማስመለስ" የሚል መፈክርም ሲያስተጋቡ ይደመጡ እንጂ የ2002 ምርጫ ጥያቄ ቢነሳ የሚሰጡት በቂ መልስ የላቸውም፡፡ ሁኔታን ሳያገናዝቡና ሊከተሉ ለሚችሉ ጥያቄዎች መልስ ለመመለስ ሳይዘጋጁ "ፈጽሞ አንሳተፍም" ብሎ መደምደሙ በእምቢተኝነት ከመፈረጁ ሌላ ምንም የፖለቲካ ብልኅነትን  አያሳይም፡፡ ወደድነው ጠላነው÷ ህገ-ወጥ ነው አልነው አላልነው  የህወሓት መንግስት ኢትዮጵያን እየገዛ ነው፡፡ ጊዜ ቆሞ እየጠበቀን አይደለም፡፡ "የግንቦቱን ድል ማስመለስ" የሚለው መፈክር አሁንም ህወሓት ፓርላማውን ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ይልቀቅ ማለት ነው ብለን የምናምን ከሆነ ከጋረደን ዳፍንት እግዜር ያድነን ብቻ ነው ለማለት የሚቻለው፡፡ ገና ዛሬ ነው ከስንት መከራና ትግል በኋላ የፓርላማ ተመራጭ የሆኑትን የቅንጅት መሪዎች ብቻ ከእስር ለማስለቀቅ የተቻለው÷ እንኳን የፓርላማውን ወንበር ማስለቀቅ ቀርቶ፡፡ ጊዜው እየሄደ ነው÷ የምርጫው ቀን እየተቃረበ ነው÷ የተቃዋሚ ድርጅቶች በዚህ የምርጫ ጥያቄ ላይ ግልፅና አስማሚ የሆነ እይታና አቋም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆን፡፡ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታዎች በሚቀጥለው ምርጫ ውስጥ ለመሳተፍ እያቆበቆቡ ያሉ ድርጅቶች አሉ፡፡ ለዚህ ነው መሟላት አለባቸው ብዬ ካቀረብኳቸው ስድሰት ነጥቦች ውስጥ *"ሁሉም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባለጉዳዮች በ2002 (በ2010 በፈረንጅ) ለሚደረገው ምርጫ ሊስማሙባቸው በሚችሉአቸው የምርጫው ደንቦችና ዝግጅቶች ላይ ውይይት እንዲጀምሩ"* የሚለውን የጨመርኩት፡፡ ይህ ከህወሓት ጋር እንስራ ይላል ከተባለ ምላሼ አይልም ነው፡፡ በምርጫ 2002 እንሳተፍ ይላል? አይልም፡፡ ታዲያ ምንድነው የሚለው? የሚለው ሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳይ ያገባናል የሚሉት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች (ኢሕአፓን ጨምሮ ማለት ነው) ምርጫውን ለማካሄድ ይሁን ላለማካሄድ የምርጫ ሁኔታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መነጋገር መጀመር አለባቸው ነው፡፡ የሚደርሱባቸው ስምምነቶች ወይም ልዩነቶች ናቸው በምርጫው ውስጥ መሳተፍን ወይም አለመሳተፍን የሚወስኑት፡፡ ያለፈው የ97 ምርጫ ሁኔታ እንዳይደገም ከተፈለገ÷ ያለፈው የተቃዋሚዎች መፍረክረክ እንዳይመለስ ከታሰበ ይህ ነው ዛሬ መደረግ ያለበት፡፡ እንዲያው ምንም ሳይዙና ምንም ሳይዘጋጁ "የግንቦቱን ድል ማስመለስ" የሚለውን መፈክር ብቻ ማስተጋባት አይበቃም፡፡ "የግንቦቱን ድል ማስመለስ" ማለት ምን ማለት ነው ተብሎ ሲጠየቅ ምንም መመለስ ያልቻለው በአምባገነኑ ክፍል ያለ አንድ የኢሕአፓ መሪ ዛሬም ድረስ ትዝ ይለኛል፡፡ ከፊታችን ተደቅኖ ባለው ሁኔታ "የግንቦቱን ድል ማስመለስ" ማለት ከላይ የጠቀስኳችውንና ኦታዋ ሄጄ ያቀረብኳቸው ስድስት ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሟሉ ማድረግ ነው፡፡ እነኝህ ስድስት ቅድመ-ሁኔታዎች ከተሟሉ ደግሞ ኢትዮጵያ ከባዱን አደጋ አለፈች ማለት ነው፡፡ እነኝህ ሁኔታዎች ከተሟሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ተወዳጅነትና ተቀባይነት ያለው የፖለቲካ ድርጅት  የፖለቲካ ስልጣኑን ተረከበ ማለት ነው፡፡ ለእነኝህ ስድስት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት መታገልን የሚቃወሙት በራሳቸውና በድርጅታቸው የሚተማመኑ ሀቀኛ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች ሳይሆኑ አገሪቱ ውስጥ ባለው የፖለቲካ ቀውስ ለመጠቀም የሚፈልጉና ባሉበት  ለመቀጠል የሚሹ ዳግም የከርሞ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ህወሓት እንግባ ያለ ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን የለም፡፡ ወደ ህወሓት መግባትንም የሚያስመርጥ የፖለቲካ እውነታ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም፡፡ ህወሓት በ97ቱ የምርጫ ሁኔታ ያሳዬው ፋሺስታዊና አሸባሪ ባህሪዩ ምንም አልተቀየረም፡፡ ከተጠቀሱት ስድሰቱና መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች ውሰጥ አንዱ እንኳን አልተሟላም፡፡

ወደ ህወሓት ሊገቡ ነው የሚለው ውሸትና ቅጥፈት ለደረሰባቸው የፖለቲካ ኪሳራ ጊዜ ለመሸመትና ግራና ቀኙን አይተውና አመዛዝነው ነጻ አቋም ለመውሰድ የማይችሉትን የዋሆችን እያደናገሩ ለመቆዬት እንደ ኑሮ ዘዴ የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ቅመራ ነው።

ወንጀዮቼ ኢሕአፓ ውስጥ በተፈጠረው ድርጅታዊ ቀውስ ምክንያት በለመዱት የፈጠራ የቅጥፈትና የስድብ "ፖለቲካቸው" በዋናነት ያነጣጠሩት በኔ ላይ ነው። ይህ ብዙም ሊያሰኬዳቸው አይችልም። ድርጅታችንን ከጥቂት የአምባገነኖች ቡድን ማላቀቅ ሰፊ የአባላት መሰረት ያለው እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴ ደግሞ ከኔ ከአንድ ግለሰብ ጋር የሚያያይዘው ምንም ነገር የለም። ድርጅቱን ከአምባገነኖች ለማጽዳት በሚደረገው ትግል ውስጥ በርካታ የማምንባቸው የማከብራቸውና የምከተላቸው የትግል ጓደኞች አሉኝ። የእንቅስቃሴያችን ህይወትና እስትንፋስ እነኝህ በግል ጥቅም ያልተጠመዱና ጎልማቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት ብቻ የሆኑ ውድ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በኔ ላይ የተከፈተው የስም ማጥፋት ዘመቻ በትግላችን ላይ የሚኖረው አሉታዊ ውጤት እምብዛም ነው። ነግ ከነገ በስቲያ የሚጋለጡትና የሚያፍሩት፥ ጎሊና ካላቸው፥ እነርሱው ራሳቸው ናቸው። እንዲያው ለሬከርዱ ያህል፥ እኔ ወያኔ ጋ ልግባ ወይም እንግባ ብዬ አላውቅም። ወያኔ ጋ እንድገባ የሚያጓጓኝ ምንም ቁሳዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ምክንያት የለኝም። ወያኔ ጋ ለመግባት ብፈልግ በኢሕአፓ በኩል መሄድ አያስፈልገኝም። ወያኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የመጣና ለኢትዮጵያ ደግ የሚመኝ ድርጅት ነው ብዬም አምኜ አላውቅም። ወያኔና የወያኔ የዘር ፖለቲካ በተባበረ የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ሊወገድ የሚገባው የትግላችን ዋነኛ ዒላማ መሆኑን ለአንድ አፍታም ዘንግቼ አላውቅም።

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጥላል፥ እኔም የበኩሌን ከማበርከት ወደኋላ አልልም!!!